30ኛ ዓመት ቁጥር 38
30th Year, No. 38

ባሕርዳር መጋቢት 25 ቀን 2018 ዓ.ም
Bahir Dar, April 3,2025

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት
ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG
of the Amhara National Region Council in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the Auspices of the Council of the Amhara National Region

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ 738.53ብር
Unit Price Birr 738.53

**አዋጅ ቁጥር ፫፻፭/፪ሺ፲፰ ዓ/ም**

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር ሥርዓትን መደንገጊያ አዋጅ**

**Proclamation No 305/2026**

**Public Projects Administration and Management System Determination Proclamation in the Amhara National Regional State**

**አዋጅ ቁጥር ፫፻፭/፪ሺ፲፰ ዓ/ም**

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር ሥርዓትን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ**

ፕሮጀክቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ በማድረግ የክልሉን ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት እንዲያፋጥኑ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ፍትሐዊ ተጠቃሚነት፣ የፕሮጀክት ቅልጥፍና እና ውጤታማነትን የሚያረጋግጥ የፕሮጀክት አስተዳደርና አመራር ሥርዓት በሕግ መደንገግ ተገቢ በመሆኑ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር መሠረታዊ ፅንሰ ሐሳቦችን፣ መርሆዎችን፣ ሂደቶች እና በሂደቶች ውስጥ የተለያዩ የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት ያላቸውን ሥልጣንና ተግባር በሕግ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

**Proclamation No 305/2026**

**A Proclamation to Provide for the Amhara National Regional State Public Projects Administration and Management System**

WHEREAS, it has been found necessary to ensure the effective implementation of public projects so as to accelerate the social and economic development of the Region;

WHEREAS, it is appropriate to provide, by law, a public projects administration and management system that ensures equitable benefits to various societies in the Region and promotes project efficiency and effectiveness;

WHEREAS, it has been found necessary to legally define the fundamental concepts, principles, procedures and powers and duties of different government executive bodies in the process of administration and management of public projects of the Government of the Amhara National Regional State;

ከክልሉ የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ የመነጩ ፕሮጀክቶችን ወይም ፕሮግራሞችን ለመፈጸም ግልጽ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት ተጠያቂነትን ማስፈን አስፈሊጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፱ ንዑስ-አንቀጽ ፫ (፩) ድንጋጌ ስር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፫፻፭/፳፻፲፰ ዓ.ም” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1/ “ፕሮጀክት” ማለት በክልሉ መንግሥት ቋሚ ሀብትን ለማፍራት ወይም ለማሻሻል፣ የክልሉን ኢኮኖሚ ለማሳደግ፣ የገበያ ክፍተቶችን ለመሙላት እና የቀጣዩን ትውልድ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በተወሰነ ሀብት፣ ጊዜና ቦታ ምርትና አገልግሎቶችን ለመስጠት በፕሮጀክት አስፈፃሚ አካላት በክልሉ መንግሥት መደበኛ በጀት፣ በአገር ውስጥና በውጭ ብድር ወይም እርዳታ የሚከናወን የመንግሥትን ዋስትና የሚጠይቅ የሥራ እቅድ ነው::



WHEREAS, it is necessary to maintain accountability by establishing a clear operational system for the implementation of projects and programs derived from the Regional medium-term plan;

NOW, THEREFORE, the Amhara National Region Council, in accordance with Article 49 (3) (A) of the Regional Constitution, is hereby proclaimed this proclamation.

## PART ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the “the Amhara National Regional State Public Projects Administration and Management System Proclamation No. 305/2026.”

### 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ “**Project**” means investments carried out by the project implementing bodies for the acquisition or improvement of fixed assets, to accelerate economic growth, adress market gaps and ensure equitable benefit of present and future generations, which is impelemnted by defined resource, time and place to provide products and services with recurrent Regional Government budget, domestic or foreign loans or aid with government guarantee.

፪/ **"ፕሮግራም"** ማለት ተዛማጅ የሆኑ ፕሮጀክቶችን በተቀናጀ መንገድ በመምራት እና በማስተዳደር ሰፊና የረጅም ጊዜ ግቦችን ለማሳካት የሚያስችል የእቅድ መርሃ-ግብር ነው::

፫/ **"የክልል መንግሥት ፕሮጀክት አስተዳደር እና አመራር ሥርዓት"** ማለት የመንግሥት ፕሮጀክት ሐሳብ ማመንጨት፣ የፕሮጀክት ፅንሰ-ሐሳብ ማዘጋጀት፣ የመጀመሪያ ደረጃ መረጣ ወይም ምልመላ፣ የቅድመ-አዋጭነትና አዋጭነት ጥናት፣ የአዋጭነት ግምገማ ማድረግ፤ ቅደም-ተከተል ማስያዝ፣ መምረጥ፤ በጀት ላይ መትከል፣ ትግበራ እና ድኅረ-ትግበራ ግምገማ መሠረታዊ መርሆች እና ዑደቶች እንዲሁም የተለያዩ የፕሮጀክት አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ኃላፊነት መለየትና መወሰንን የሚመራ ሥርዓት ነው::

፬/ **"የፕሮጀክት አስፈፃሚ አካላት"** ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ከፅንሰ-ሐሳብ ማመንጨት ጀምሮ እስከ ማስተዳደር ባለው ዑደት ውስጥ የሚሳተፉ የክልሉ መንግሥት ፕሮጀክት አስፈፃሚ ተቋማትና የልማት ድርጅቶች ናቸው::

፭/ **"የፕሮጀክት ፅንሰ-ሐሳብ"** ማለት የመነጨውን የፕሮጀክት ሐሳብ ለመወሰን ወይም ወደ ቀጣይ ዑደት ለመውሰድ በዋና ዋና መሠረታዊ የፕሮጀክት ዝግጅት መስፈርቶች መሠረት የሚዘጋጅ ሰነድ ነው::

2/ **"Program"** means a planning framework that enables the coordinated administration and management of related projects in order to achieve broad and long-term objectives.

3/ **"Regional Government Public Projects Administration and Management System"** means a system in which project identification, developing project concept notes, preliminary screening, preparation of pre-feasibility and feasibility studies, appraisal of feasibility studies, prioritization, selection, budgeting, implementation and ex-post evaluation of public projects as well as identifying and determining the duties and responsibilities of different project implementing bodies is managed.

4/ **"Project Executive Organs"** means regional government executive organs and public enterprises that participate at any stage of the project cycle, from project identification to administration.

5/ **"Project Concept Note"** means a document prepared in accordance with the basic project preparation criteria to set out the initial project idea or to advance the project to the next stage of project cycle.

፮/ **"የፕሮጀክት የመጀመሪያ ደረጃ መረጣ ወይም ምልመላ"** ማለት የተዘጋጀውን የፕሮጀክት ፅንሰ-ሐሳብ መርምሮ ፕሮጀክቱ ወደ ቅድመ አዋጭነት ወይም አዋጭነት ጥናት ወይም በቀጥታ ወደ ቅደም ተከተል ማስያዝ፣ መምረጥ እና በጀት ላይ መትከል ዑደት ሊሄዱ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን መለየትና መወሰን ነው::

፯/ **"የፕሮጀክት ዝርዝር አዋጭነት ጥናት"** ማለት የፕሮጀክቱን አዋጭነት ለመወሰን የፕሮጀክቶችን መሠረታዊ ይዘቶች ማለትም የፋይናንስ፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ አዋጭነት፣ የቴክኒክ አግባብነት እና አካባቢያዊ ተፅዕኖ ግምገማ በአካተተ መልክ እንደፕሮጀክቱ ባሕሪ የሚከናወን ጥናት ነው::

፰/ **"የፕሮጀክት አዋጭነት ግምገማ"** ማለት አንድ የፕሮጀክት ዝርዝር የአዋጭነት ጥናት የፋይናንስ፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ፣ የአዋጭነት የቴክኒካል አግባብነት እና የአካባቢዊያዊ ተስማሚነት በማረጋገጥ ፕሮጀክቱ ለትግበራ ብቁ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚደረግ ግምገማ ነው::

፱/ **"የፕሮጀክት ገለልተኛ የአዋጭነት ግምገማ"** ማለት ፕሮጀክቱን ካቀረበው ወይም ከሚተገብረው አስፈፃሚ አካል ውጭ በሆነ በዚህ አዋጅ ሥልጣን በተሰጠው አካል በፕሮጀክቱ አዋጭነት ጥናት ላይ የሚደረግ የጥራት ማረጋገጫ ግምገማ ነው::

፲/ **"የፕሮጀክት ቅደም ተከተል በማስያዝና በመምረጥ በጀት ላይ መትከል"** ማለት በአዋጭነት ግምገማ መሠረት አዋጭነቱ የተረጋገጠ አዲስ የመንግሥት ፕሮጀክትን ከዓመታዊ በጀት ፍላጎትና አቅርቦት አንፃር ቅድሚያ የሚያገኘውን መምረጥና ማፅደቅ ነው::

6/ **"Preliminary Project Selection or Screening"** means a process of reviewing project concept notes with a view to identifying and determining whether projects should proceed to the pre-feasibility or feasibility study phase, or proceed directly to the prioritization, selection, and budgeting cycle.

7/ **"Project Feasibility Study"** means a study conducted to examine the feasibility of a project in terms of its basic elements, including financial, economic, social, technical appropriateness, and including environmental impact assessment as per characteristic of the project.

8/ **"Project Feasibility Appraisal"** means an appraisal undertaken to determine whether or not a project is viable after ensuring same in terms of its financial, economic, social, technical aspects, and environmental assessment.

9/ **"Independent Project Feasibility Review"** means a quality assurance evaluation undertaken by an independent body, other than the body that proposed or will implement the project, which is authorized under this Proclamation to evaluate the project feasibility study.

10/ **"Project Budgeting by Prioritization and Selection"** means the process of prioritizing and selecting a new public project for budgeting, provided that the project has been proven viable based on a feasibility assessment and is given priority according to annual budget needs and availability.

፲፩/ **"የፕሮጀክት የትግበራ ዕቅድ"** ማለት አዋጭነቱ ተረጋግጦ፣ ተመርጦ እና ቅደም ተከተል ተይዞለት በበጀት ላይ እንዲተከል የተመረጠ ፕሮጀክት በበጀት ከመካተቱ በፊት አስፈላጊው የትግበራ ቅድመ ሁኔታ ማማሏቱን ለማረጋገጥ በአስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች የሚዘጋጅ የፕሮጀክት ትግበራ የፊዚካልና የፋይናንስ እቅድ መርሐ-ግብር ነው::

፲፪/ **"የፕሮጀክት ትግበራ"** ማለት አዋጭነቱ ተረጋግጦ በጀት የተመደበለትን የመንግሥት ፕሮጀክት ምርት ወይም አገልግሎት የሚሰጥበት ደረጃ ለማድረስ የሚደረግ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ነው::

፲፫/ **"የፕሮጀክት ክትትልና አፈፃፀም ግምገማ"** ማለት በፕሮጀክቱ የታቀዱ ተግባራት በታቀደው ጊዜ፣ ወጭ፣ መጠንና ጥራት መከናወናቸውን ለማረጋገጥ ወቅታዊ ወይም ተከታታይ የትግበራ አፈፃፀም ክትትል የሚደረግበት ሂደት ነው::

፲፬/ **"የፕሮጀክት ክለሳ"** ማለት ከቁጥጥር ውጭ በሆኑ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ክስተቶች ምክንያቶች በመተግበር ላይ ያለ እንዲሁም ለትግበራ በተዘጋጀ ፕሮጀክት ላይ የሚደረግ ማንኛውንም የማስተካከያ ወይም የማሻሻያ ሥራን የሚያካትት ነው::

፲፭/ **"የፕሮጀክት ትግበራ ማጠናቀቂያ ግምገማ"** ማለት ፕሮጀክቱ በውል መሠረት የፕሮጀክቱ ጥራት፣ ጊዜ እና ወጪ ባስጠበቀ መልክ ተግባራዊ ተደርጎ መጠናቀቁን ለማረጋገጥ የሚደረግ ግምገማ እና የግምገማ ማጠቃለያ ሪፖርት ነው::

11/ **"Project Implementation Plan"** means a physical and financial plan prepared by project implementing bodies for a project that has been appraised, confirmed to be viable, selected and prioritized for budgeting, in order to ensure that the necessary preconditions for implementation have been met before budgeting.

12/ **"Project Implementation"** means the process of executing a project which has been appraised and confirmed to be viable and for which budget has been allocated to a stage where it can provide goods or services.

13/ **"Project Monitoring and Implementation Evaluation"** means the process of conditional or progress monitoring of implementation of planned project activities to make sure that they are carried out as per the planned time, cost and quality.

14/ **"Project Revision"** means any change or modification undertaken on a project force majeure resulting from man made or natural disasters at the implementation or formulation phase.

15/ **"Project Implementation Completion Evaluation"** means an assessment carried out to verify that a project implementation has been completed on aggrement maintaining projects quality, time and expenditure, and summary report prepared based on such assessment.

፲፮/ **“የፕሮጀክት ርክክብ”** ማለት ፕሮጀክቱ ሲሰጥ የታሰበውን ምርት ወይም አገልግሎት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ መስጠት ሲችል ወይም የሚሰጥበት ደረጃ ላይ ሲደርስ በውል ሰጪ እና ውል ተቀባይ መካከል የሚደረግ የፕሮጀክት ርክክብ ሂደት ነው::

፲፯/ **“የፕሮጀክት ድኅረ-ትግበራ ግምገማ”** ማለት ፕሮጀክቱ ተጠናቆ ወደ ሥራ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በዚህ አዋጅ ከተወሰነ የጊዜ ገደብ በኋላ ፕሮጀክቱ የታለመለትን ዓላማ እያሳካ መሆን አለመሆኑን በመገምገም የተገኘውን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አከባቢያዊ ፋይዳ ለመለየት የሚደረግ ግምገማ ነው::

፲፰/ **“አስቸኳይ ፕሮጀክት”** ማለት ለክልሉ ፀጥታና ደኅንነት እንዲሁም በሰው ሠራሽ ወይም በተፈጥሮ ምክንያት የሚከሰት አደጋን ለመከላከልና ለመቋቋም በአጣዳፊነት የሚተገበር የመንግሥት ፕሮጀክት ነው::

፲፱/ **“የበጀት ጥሪ”** ማለት የክልሉን የፊሲካልና የኢኮኖሚ ማዕቀፍ ታሳቢ ተደርገው የሚወሰዱ ጉዳዮችን ባገናዘበ መልኩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚያስፈልጋቸን ዓመታዊ በጀት አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ በገንዘብ ቢሮ የሚደረግ ጥሪ ነው::

፳/ **“የፕሮጀክት ጽንሰ-ሐሳብ ወይም የፕሮጀክት የአዋጭነት ጥናት አቀራረብ”** ማለት የፕሮጀክት አስፈፃሚ አካላት የፕሮጀክት ጽንሰ-ሐሳብ ወይም የአዋጭነት ጥናት የተደረገበትን ሰነድ ለፕላንና ልማት ቢሮ የሚያቀርቡበት ሂደት ነው::

16/ **“Project Handover”** means the process of transferring a project from the contractor to the project owner when the project has begun delivering, in whole or in part, the intended product or service, or has proved reached such a stage.

17/ **“Post-Implementation Project Evaluation”** means an evaluation conducted after the project has been completed and put into operation, within a period specified in this Proclamation, to determine whether the project is achieving its intended objectives and to assess the social, economic, and environmental impacts it has generated.

18/ **“Emergency Project”** means a public project implemented on an emergency basis for the security and safety of the region, as well as to prevent and respond to man-made or natural disasters.

19/ **“Budget Call”** means a call issued by the Bureau of Finance to government offices to prepare and submit their annual budget proposals, taking into account matters related to the Region’s fiscal and economic framework.

20/ **“Project Concept or Project Feasibility Study Submission”** means the process by which project implementing entities submit a project concept or feasibility study document to the Bureau of Planning and Development.

፳፩/ “ሰው” ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው::

፳፪/ በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ያካትታል::

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

፩/ ይህ አዋጅ በፕሮጀክት አስፈፃሚ አካላት በሚተገበሩ የክልሉ መንግሥት ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ይህ አዋጅ ለክልሉ ፀጥታና ደኅንነት፣ አስቸኳይ ሰው ሠራሽ ወይም የተፈጥሮ አደጋን ለመከላከል ወይም ለክልሉ ሕዝብ ጥቅም ሲባል በልዩ ሁኔታ በአስፈጻሚ አካላት ቀርቦ በመስተዳደር ምክር ቤት ውሳኔ በሚተገበሩ እንዲሁም ከልማት አጋር ድርጅቶች ጋር በሚደረግ ልዩ ስምምነት በሚመሩ ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም::

## ፬. ዓላማ

ይህ አዋጅ የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡-

፩/ በፕሮጀክት ዑደት ውስጥ አስፈፃሚ አካላት ያላቸውን ሥልጣንና ኃላፊነት በግልፅ በማስቀመጥ ግልፀኝነትን እና ተጠያቂነትን በማስፈን የክልሉ መንግሥት ፕሮጀክቶች ወይም ፕሮግራሞች በታለመላቸው ጊዜ፣ ወጭ እና ጥራት በመፈጸም ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ፤

21/ “**Person**” shall mean any physical or juridical person.

22/ Any expression in the masculine gender in this Proclamation includes the feminine.

## 3. Scope of Application

1/ This Proclamation shall apply to all projects and programs of the Regional Government that are executed by project implementing bodies.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-article (1) of this Article, this Proclamation shall not apply to projects and programs executed by executive bodies under exceptional circumstances pursuant to a decision of the Regional Government Council, for the security and safety of the Region, prevention of imminent man-made or natural disasters or the welfare of people of the Region, nor to projects and programs implemented under special agreements with development partner organizations.

## 4. Objective

This Proclamation has the following objectives:

1/ To ensure that projects are carried out as per the planned time, cost and quality by clearly defining the Powers and Duties of different project implementing bodies in project cycle and ensuring accountability and transparency;

፪/ ፕሮጀክቶች ወይም ፕሮግራሞች ከዝግጅት እስከ ትግበራ የሚከተሏቸው ዑደቶች እና በዑደቶች ላይ ተግባራዊ መደረግ ያለባቸውን መርሆዎች በግልፅ ማስቀመጥ፤

፫/ ለፕሮጀክቶች ወይም ለፕሮግራሞች የሚመደብ ሀብት አጠቃቀምን በማጎልበት ፕሮጀክቶች ወይም ፕሮግራሞች የታለመላቸውን ዓላማ እንዲያሳኩ በማድረግ የኅብረተሰቡን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ::

## ክፍል ሁለት

## የፕሮጀክት አስተዳደር እና አመራር ሥርዓት ዑደቶች

### ፭. የፕሮጀክት ምደባ

፩/ የምደባ ዝርዝሩን በተመለከተ መስተዳድር ምክር ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ሆኖ ማንኛውም ፕሮጀክት ከሚከተሉት ደረጃዎች በአንዱ የሚመደብ ይሆናል፦

ሀ) ከፍተኛ ፕሮጀክት፤

ለ) መካከለኛ ፕሮጀክት፤

ሐ) አነስተኛ ፕሮጀክት::

፪/ ማንኛውም የፕሮጀክት አስፈፃሚ አካል ሌሎች የአሠራር ሂደቶችን ለማስቀረት ወይም ለማለፍ ብሎ የፕሮጀክቶችን ምደባ አሳንሶ ካቀረበ ፕሮጀክቱ ውድቅ ይሆናል::

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም የፕሮጀክት አስፈፃሚ አካል ፕሮጀክትን በምዕራፍ ከፋፍሎ ማቅረብ ይችላል::

2/ To clearly define cycles that projects and programs shall follow from formulation to implementation and the principles which shall be applicable to such cycles;

3/ To ensure that projects are socially and economically effective and achieve their objectives by optimizing the use of resources allocated to projects and programs.

## PART TWO

## PROJECTS ADMINISTRATION AND MANAGEMENT SYSTEM CYCLES

### 5. Project Categories

1/ Subject to details to be determined by a Regulation to be issued by the Regional Government Council, every project shall fall under one of the following categories:

A) Large project;

B) Medium project;

C) Small project.

2/ Where a project implementing body submits an understated project category with the intent to circumvent or bypass other operational procedures, the project shall be rejected.

3/ Notwithstanding the provision of Sub-article (2) of this Article, a project implementing body may submit a project in phases.

## ፮. ስለፕሮጀክት ፍትሐዊነት

፩/ ፕሮጀክቶች ወይም ፕሮግራሞች የኅብረተሰቡን ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ መልኩ የሚተገበሩ ይሆናል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ላይ ከተደነገገው የፍትሐዊነት መርህ በመነሣት ፕሮጀክቶችንና ፕሮግራሞችን በፍትሐዊነት ለመደልደል የሚያስችል የፕሮጀክት መደልደያ ቀመር መስተዳደር ምክር ቤቱ ሊያወጣ ይችላል።

## ፯. የፕሮጀክት ዑደቶች

፩/ ማንኛውም ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም የዝግጅት፣ የትግበራ እና ድኅረ-ትግበራ ዑደቶች ይኖሩታል::

፪/ የፕሮጀክቶች ወይም የፕሮግራሞች የዝግጅት ሂደት የሚከተሉት ንዑስ -ዑደቶች ይኖረዋል:-

ሀ) የፕሮጀክት ወይም የፕሮግራም ልየታ እና የመጀመሪያ ደረጃ መረጣ ወይም ምልመላ፤

ለ) የፕሮጀክት ወይም የፕሮግራም ቅድመ-አዋጭነት እና አዋጭነት ጥናት፤

ሐ) ፕሮጀክቱ ወይም ፕሮግራሙ በሚመለከተው አስፈጻሚ አካል የሚደረግ የአዋጭነት ግምገማ እና የገለልተኛ የአዋጭነት ግምገማ፤

መ) ፕሮጀክቶችን ወይም ፕሮግራሞችን ቅደም ተከተል ማስያዝ፣ መምረጥ፣ እና በጀት መትከል::

## 6. Project Equitablity

1/ Projects and programs shall be implemented in a manner that ensures equitable benefits to the society.

2/ Based on the principle of equity set forth in Sub-article (1) of this Article, the Regional Government Council may prescribe a project allocation formula appropriate for the equitable distribution of projects and programs.

## 7. Project Cycles

1/ Any project or program shall have the formulation, implementation and post-implementation cycles.

2/ The formulation cycle of projects or programs shall have the following sub-cycles:

A) Project or program identification and preliminary selection or screening;

B) Project or program pre-feasibility and feasibility study;

C) Projetct or program Feasibility Appraisal and Independent Feasibility Review carried out by concerned Executive Organ.

D) Project or program prioritization, selection and budgeting.

፫/ የፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም የትግበራ እና ድኅረ-ትግበራ ሂደት የሚከተሉት ንዑስ -ዑደቶች ይኖራቸዋል፡-

ሀ) የፕሮጀክት ወይም የፕሮግራም ትግበራ፣ ክለሳ፣ ክትትል፣ ግምገማ እና ሪፖርት፤

ለ) የፕሮጀክት ወይም የፕሮግራም ርክክብ፣ የማጠቃለያ ግምገማ እና ሀብት ምዝገባ፤

ሐ) ፕሮጀክቶችን ወይም ፕሮግራሞችን ወደ ምርት ወይም አገልግሎት ወደ መስጠት ማስገባት እና ማስቀጠል፤

መ) የፕሮጀክቶች ወይም የፕሮግራሞች ድኅረ-ትግበራ ግምገማ::

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ (፪) እና (፫) የተደነገገው ቢኖርም አንድ ፕሮጀክት የፕሮጀክት ዑደቶችን ሳይጠብቅ ወደ ትግበራ እንዲገባ ሊደረግ ይችላል፤ ዝርዝሩ መስተዳደር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል::

፭/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ (፬) ድንጋጌ ቢኖርም የአንድ ፕሮጀክት ፅንሰ-ሐሳብ ተዘጋጅቶ ለመጀመሪያ ደረጃ መረጣ ወይም ምልመላ ቀርቦ ተቀባይነት ካላገኘ ወደ ቀጣይ ሂደት ሊሸጋገር አይችልም::

፮/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ (፪) እና (፫) ስር የተዘረዘሩት የፕሮጀክት ዑደት ይዘት፣ መስፈርት፣ አቀራረብና አፀዳደቅን በተመለከተ ዝርዝሩ መስተዳደር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል::

3/ Project or program implementation and post-implementation cycles shall have the following sub-cycles:

**A)** Project or program implementation, revision, monitoring, evaluation and reproting;

**B)** Project or program handover, completion assessment and assets registration;

**C)** Evolution of projects or programs to product or service delivery and continuation;

**D)** Projects and programs post-implementation evaluation.

4/ Notwithstanding the provisions of Sub-articles (2) and (3) of this Article, a project may be implemented without following the prescribed project cycles; the details shall be determined by a Regulation to be issued by the Government Council.

5/ Notwithstanding the provision of Sub-article (4) of this Article, where a project concept has been prepared and submitted to the first stage of selection or screening and is not approved, it shall not proceed to the next stage of the project cycle.

6/ The details of the content, criteria, submission and approval of the project cycles set out under Sub-articles (2) and (3) of this Article shall be determined by a Regulation to be issued by the Government Council.

# ክፍል ሦስት

## የፕሮጀክት ዝግጅት፣ የትግበራ እና የድኅረ ትግበራ ዑደቶች መሠረታዊ መርሆዎች

### ፰. የፕሮጀክት ልየታ እና የመጀመሪያ ደረጃ መረጣ ወይም ምልመላ

፩/ ማንኛውም ፕሮጀክት አስፈፃሚ አካል ላመነጨው ፕሮጀክት ለውሳኔ አሰጣጥ እና ለመጀመሪያ ደረጃ መረጣ ወይም ለምልመላ በሚያግዝ መልኩ የፕሮጀክት ፅንሰ-ሐሳብ ማዘጋጀት አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም ፕሮጀክት በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፯ መሠረት በፕሮጀክት የማመንጨት ሂደት መሠረታዊ ተብለው የተለዩ መስፈርቶች ተሟልተው ሲቀርቡ ብቻ ወደ መጀመሪያ ደረጃ መረጣ ወይም ምልመላ ሂደት ይገባል፡፡

፫/ ማንኛውም ፕሮጀክት ወደ ቅድመ አዋጭነት ወይም አዋጭነት ጥናት፣ ወደ ቅደም ተከተል ማስያዝ እና ወደ መረጣ ዑደት ሊተላለፍ የሚችለው በፕሮጀክቶች ገለልተኛ አዋጭነት ግምገማ መሠረት ተቀባይነት ካገኘ ብቻ ነው፡፡

### ፱. የፕሮጀክት ቅድመ አዋጭነት እና አዋጭነት ጥናት

፩/ በመጀመሪያ ደረጃ መረጣ የተመለመለ መካከለኛ ወይም ከፍተኛ ፕሮጀክት ወደ ሥራ ከመግባቱ በፊት የአዋጭነት ጥናት መደረግ አለበት፤



# PART THREE

## FUNDAMENTAL PRINCIPLES OF PROJECT FORMULATION, IMPLEMENTATION AND POST-IMPLEMENTATION CYCLES

### 8. Project Identification and Preliminary Selection or Screening

1/ Any project implementing body shall prepare a project concept note for project ideas identified by it, in a manner that is suitable for decision-making and for preliminary selection or screening.

2/ Any project shall proceed to preliminary selection or screening only if it meets the basic criteria specified in the project generation cycle under Article 7 of this Proclamation.

3/ Any project shall only proceed to prefeasibility or feasibility study, prioritization and selection cycles where it has been accepted through independent project feasibility review.

### 9. Project Pre-Feasibility and Feasibility Study

1/ A feasibility study shall be carried out for any large or medium project which has passed preliminary screening before it is implemented;

፪/ የፕሮጀክት አስፈፃሚ አካላት ከክልሉ የሴክተር መካከለኛ እና የረጅም ዘመን እቅዶች በመነሣት ከክልሉ መንግሥት ዓመታዊ በጀት ምንጮች ውጭ የፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናቶችን በማከናወን ለገለልተኛ ግምገማ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

## ፲. የአዋጭነት ግምገማ እና በገለልተኛ ወገን የሚደረግ የአዋጭነት ግምገማ

፩/ በፕሮጀክት አስፈፃሚ ተቋም የአዋጭነት ጥናት የተደረገበት ፕሮጀክት በዚህ አዋጅ ሥልጣን በተሰጠው አካል ገለልተኛ የአዋጭነት ግምገማ መደረግ አለበት፤

፪/ የፕሮጀክት የአዋጭነት ጥናት ለገለልተኛ ግምገማ አቀራረብ የጊዜ ሰሌዳ ከዓመታዊ የክልሉ መንግሥት የበጀት ጥሪ በፊት ይሆናል፤ ዝርዝሩ በመስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት የሚወሰን ይሆናል፤

፫/ በገለልተኛ አካል ተገምግሞ አዋጭነቱ የተረጋገጠ ፕሮጀክት ከክልሉ መንግሥት ዓመታዊ በጀት ጥሪ በፊት ተመርጦ ቅደም ተከተል መያዝ አለበት፤

፬/ አንድ ፕሮጀክት የአዋጭነት ግምገማ ተደርጎበት ሳይመረጥ እና ቅደም ተከተል ሳይዝ በበጀት ላይ አይተከልም፤

፭/ በገለልተኛ አካል የአዋጭነት ግምገማ የተደረገበት እና አዋጭነቱ የተረጋገጠ ፕሮጀክት ወደ ቅደም ተከተል ማስያዝ፣ መረጣ እና በጀት ምደባ ሂደት ይሸጋገራል፡፡



2/ Project implementing bodies may, based on the region's long term and medium-term plans for each sector, carry out feasibility studies for projects outside regional government annual budget sources and submit same for independent project review.

## 10. Project Appraisal and Independent Project Review

1/ Any project on which a feasibility study has been carried out by any project implementing body shall be subject to an independent project review by a body authorized under this Proclamation;

2/ The time schedule for submitting project feasibility studies for independent review shall be before the annual regional government budget call; the details shall be determined by Regulation of the the Government Council;

3/ Any project which has been reviewed by an independent body and confirmed to be viable shall be selected and prioritized before the regional government annual budget call;

4/ A project shall not be budgeted without being appraised, selected and prioritized;

5/ Any project which has been reviewed by an independent body and confirmed to be viable shall move to prioritization, selection and budgeting.

## ፲፩. ፕሮጀክትን ቅደም ተከተል ማስያዝ፣ መረጣ እና ፕሮጀክቱን በበጀት ላይ ስለ መትከል

የፕሮጀክት መረጣ፣ ቅደም ተከተል ማስያዝ እና በጀት ላይ መትከል በሚከተለው መልክ ይከናወናል፡-

፩/ በአዋጭነት ግምገማ አዋጭ ተብሎ የተለየ ፕሮጀክትን በጀት ለመመደብ የክልሉን የብድር ጫና፣ የማክሮ ኢኮኖሚው ሁኔታ እና ሌሎች ጉዳዮችን ባማከለ መልኩ ፕሮጀክትን በመምረጥና ቅደም-ተከተል በማስያዝ በበጀት ላይ እንዲተከል የውሳኔ ሐሳብ ይቀርባል፤

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ (፩) መሠረት ተመርጠውና ቅደም ተከተል ይዘው የቀረቡት ፕሮጀክቶች በመካከለኛ ዘመን የበጀት ማዕቀፍ እና በዓመታዊ በጀት ውስጥ እንዲካተቱ ይደረጋል፤

፫/ ተመርጠው ቅደም ተከተል ይዘው በዓመታዊ በጀት የተካተቱ ፕሮጀክቶች በየደረጃቸው ለሚመለከታቸው አካላት መቅረብ እና መፅደቅ አለባቸው፤

፬/ በፕሮጀክት አስፈፃሚ አካላት በአገር ውስጥ እና በውጭ ብድር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ወይም ፕሮግራሞች አዋጭነታቸው ተገምግሞ ሲረጋገጥ ብቻ ተግባራዊ መደረግ አለባቸው፡፡

## 11. Project Prioritization, Selection and Budgeting

Project selection, prioritization and budgting shall be carried out as follows:

1/ In order to allocate budget for a project which has been appraised and identified as viable, a project shall be selected and prioritized and recommended for budgeting taking into consideration of the regions's debt burden, macro-economic conditions and other factors;

2/ Projects selected and prioritized as per Sub-article (1) of this Article shall be included in the medium-term budget framework and annual budget;

3/ Projects which have been selected, prioritized and included in the annual budget shall be submitted to the appropriate bodies at different levels and get approved;

4/ Projects or programs financed by domestic and foreign loans by project implementing bodies should only be implemented after their feasibility has been assessed and confirmed.

## ፲፪. የፕሮጀክት ትግበራ፣ ክለሳ፣ የአፈፃፀም ክትትል እና ግምገማ

፩/ ማንኛውም ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ሲተገበር አካባቢያዊ፣ ክልላዊ፣ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ሕጎችን፣ ደረጃዎችን እና ቅደም ተከተሎችን ባማከለ መልኩ መሆን አለበት፤

፪/ ከፕሮጀክት ወይም ከፕሮግራም መደበኛ ክትትል በተጨማሪ ፕሮጀክቱ ከደረሰበት አፈፃፀም ደረጃ አኳያ በዋናነት የፕሮጀክቱ አፈፃፀም ፶ በመቶ ወይም በመካከለኛ ዘመን እንዲሁም ፕሮጀክቱ ተጠናቆ ርክክብ በሚካሄድበት ወቅት መገምገም ይኖርበታል፤

፫/ እንደ ፕሮጀክቱ ወይም ፕሮግራሙ ውስብስብነት እና የትግበራ መርሃ-ግብር ርዝመት በአንዳንድ የክልሉ መንግሥት ፕሮጀክቶች ወይም ፕሮግራም ላይ የመካከለኛ ዘመን ግምገማ ይዘት ያለው ተጨማሪ ግምገማ በፕሮጀክት ወይም በፕሮግራም ትግበራ ዘመን ሊከናወን ይችላል፤

፬/ የፕሮጀክቱ ወይም የፕሮግራሙ ወሰን "የተቀየረ ከሆነ፣ በፕሮጀክቱ ወይም በፕሮግራሙ ላይ ከቁጥጥር ውጭ በሆኑ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ክስተቶች ምክንያት ፕሮጀክቱን ወይም የፕሮግራሙ መከለስ የሚያስገድድ ሁኔታ ከተፈጠረ የፕሮጀክት ወይም የፕሮግራም ክለሳ ሊፈቀድ ይችላል::

፭/ አንድ ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም በግዥና ንብረት አስተዳደር ሕግ መሠረት ክለሳ ማድረግ ከተፈቀደው መጠን በላይ የዋጋ ጭማሪ የሚያስፈልገው ከሆነ ፕሮጀክቱ ወይም ፕሮግራሙ ተዘጋጅቶ በድጋሚ የአዋጭነት ግምገማ ተደርጎበት መከለስ ይኖርበታል፤



## 12. Project Implementation, Revision, Monitoring and Evaluation

1/ Any project shall be implemented in a manner that takes into account local, regional, national and international laws, standards, and priorities;

2/ In addition to the regular project or program monitoring, based on its progress, any project shall mainly be evaluated up on 50% completion or midterm and upon completion and handover;

3/ Subject to the complexity and implementation schedule of a project or program, an additional evaluation similar to a mid-term evaluation on some regional government projects or program may be conducted during the implementation period of projects or program;

4/ Revision of a project or program may be permitted where there is a change in the scope of the project or program, or where force majeure events arising from natural or man-made circumstances occur and necessitate such revision.

5/ Where a project or program requires a cost increase beyond the limit permitted for revision under the Regional Procurement and Property Administration Law, the project or program shall be revised only after reformulation and reappraisal;

፮/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ (፭) መሠረት የክለሳ ጥያቄ ቀርቦበት በድጋሚ በሚደረግ የአዋጭነት ግምገማ መሠረት ተቀባይነት ያገኘ ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ለውሳኔ ሰጭ አካላት ቀርቦ መፅደቅ አለበት፡፡

## ፲፫. የፕሮጀክት ርክክብ፣ የማጠቃለያ ግምገማ እና የሀብት ምዝገባ

፩/ የፕሮጀክት ወይም የፕሮግራም ርክክብ ሂደት ፕሮጀክቱ በተያዘለት ውል መሠረት መከናወኑን በሚያረጋግጥ መልኩ መከናወን አለበት፤

፪/ ፕሮጀክቱ ወይም ፕሮግራሙ በውል መሠረት የፕሮጀክቱ ወይም የፕሮግራሙ ጥራት፣ ጊዜ እና ወጪ ባስጠበቀ መልክ ተግባራዊ ተደርጎ መጠናቀቁን የሚያረጋግጥ የማጠቃለያ ግምገማ እና ሪፖርት መቅረብ አለበት፤

፫/ ፕሮጀክቱ ወይም ፕሮግራሙ ከተጠናቀቀና ተገቢው ርክክብ ከተደረገ በኋላ አግባብ ባለው አካል የክልሉ መንግሥት ሀብት ሆኖ ይመዘገባል፡፡

## ፲፬. ፕሮጀክት ወደ ምርት ወይም አገልግሎት ስለማስገባት እና ስለማስቀጠል

፩/ ተጠናቆ ርክክብ የተደረገበት ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ወደ ሥራ ለማስገባት እና ለማስቀጠል የቅድመ-ዝግጅት ሥራዎች በታቀደ መልኩ መከናወን አለባቸው፤

፪/ የክልሉ መንግሥት አንድን ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም በወቅቱ ወደ ምርት ወይም አገልግሎት ማስገባት የሚያስችል በጀት የመመደብ ኃላፊነት አለበት፡፡

6/ Any project or program for which a request for revision has been submitted and has been reappraised and approved in accordance with Sub-article (5) of this Article shall be submitted to the appropriate decision-making bodies for final approval.

## 13. Project Handover, Completion Review and Assets Registration

1/ The project or program handover process shall be carried out in a manner that ensures the project is implemented in accordance with the agreement;

2/ A final evaluation and report shall be submitted to confirm that the project or program has been implemented and completed in accordance with the contract and within the approved quality, time and cost parameters;

3/ Once a project or program has been completed and properly handed over; it shall be registered as the asset of the Regional Government by the appropriate body.

## 14. Moving a Project to Production or Service Provision and Continuation

1/ Preparatory works shall be carried out in a planned manner to move a project which has been completed and handed over to operation and continuation;

2/ The Regional Government shall be responsible for allocating the budget necessary to ensure that a project is brought into production or service provision in a timely manner.

## ፲፭. የፕሮጀክት ድኅረ-ግምገማ

ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች ተጠናቀው ወደ ሥራ ከገቡ ቢያንስ ከ፪ ዓመት ቢበዛ ከ፭ ዓመት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ በተመረጡ ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች ላይ የድኅረ-ትግበራ ግምገማ መከናወን አለበት፡፡

## ፲፮. የፕሮጀክት መረጃ አያያዝ እና አስተዳደር

፩/ ማንኛውም ፕሮጀክት አስፈፃሚ አካል የሚከታተለውን ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ከፅንሰ-ሐሳብ ጀምሮ እስከ ትግበራ ድረስ ያለውን መረጃ ደኅንነቱ በተረጋገጠ የመረጃ ቋት የመያዝ እና ለፕላንና ልማት ቢሮ የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፤

፪/ ፕላንና ልማት ቢሮ በአስፈጻሚ አካል ተገንብቶ የተጠናቀቀ ማንኛውም ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም የኬክሮስና ኬንትሮስ ፍፁማዊ መገኛን ጨምሮ ፕሮጀክቱን በተመለከተ ሌሎች ሙሉ መረጃዎች በተዘጋጀው የመረጃ ቋት አደራጅቶ የመያዝ ኃላፊነት አለበት፡፡

# ክፍል አራት
# የፕሮጀክት አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር

## ፲፯. የወል ሥልጣንና ተግባራት

በሌላ ሕግ የተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል መንግሥት ፕሮጀክት አስፈፃሚ አካላት፦

፩/ በራሱ ወይም በተጠሪ ተቋም የመነጨ ፕሮጀክት ወይም የፕሮግራም ፅንሰ-ሐሳብ እና የአዋጭነት ጥናት አግባብ ባለው የአሠራር ሥርዓት መሠረት አዘጋጅቶ ያቀርባል፤



## 15. Project Post Evaluation

Post-implementation evaluation shall be carried out on selected projects and programs no earlier than two years and no later than five years after the project or program has been completed and become operational.

## 16. Handling and Administration of Project Information

1/ Any project implementing body shall maintain a secured database of information on each project or program it monitors, from the project concept note until implementation, and shall submit such information to the Planning and Development Bureau;

2/ The Planning and Development Bureau shall the responsibility to organize and maintain a database of all projects and programs completed by executive bodies, including their absolute location of latitude and longitude coordinates.

# PART FOUR
# POWERS AND DUTIES OF PROJECT IMPLEMENTING BODIES

## 17. Common Powers and Functions

Without prejudice to the powers and functions given them by other laws, the regional project executive bodies shall;

1/ Prepare and submit, in accordance with the applicable procedures, a project or program concept note and feasibility study for any project or program initiated by it or by an institution accountable to it;

፪/ የአዋጭነት ጥናት የተደረገበትን ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም በራሱ አቅም የአዋጭነት ግምገማ በማካሄድ ጥራቱን ያረጋግጣል፤ የአዋጭነት ግምገማ ሪፖርት ለፕላንና ልማት ቢሮ ያቀርባል፤

፫/ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ክለሳ እንዲደረግባቸው ውሳኔ የተሰጠባቸውን ፕሮጀክቶች ክለሳ በማድረግ ለፕላንና ልማት ቢሮ በማቅረብ በመስተዳደር ምክር ቤቱ በኩል ውሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል፤

፬/ በሕግ ከተሰጠው መጠን በላይ ክለሳ ለሚጠይቅ ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም የክለሳ ጥያቄ በማዘጋጀት ለፕላንና ልማት ቢሮ በማቅረብ በመስተዳደር ምክር ቤቱ በኩል ውሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል፤

፭/ ለአዋጭነት ግምገማ የሚቀርብ እና ተግባራዊ እንዲሆን ውሳኔ የተሰጠበት ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ከመተግበሩ በፊት የትግበራ ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላቱን ያረጋግጣል፤

፮/ ተመርጦ ቅደም ተከተል ለተያዘለት ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም የአዋጭነት ጥናትን መሠረት በማድረግ የፕሮጀክት ወይም የፕሮግራም ትግበራ እቅድ በማዘጋጀት ለውሳኔ ለፕላንና ልማት ቢሮ ያቀርባል፤

፯/ በፕሮጀክት ወይም በፕሮግራም ዝግጅት፣ አዋጭነት ግምገማ፣ ትግበራና ክትትል ዑደት በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት፤

ሀ) የፕሮጀክት ወይም የፕሮግራም አስፈላጊ መጠቀሚያዎችና መገልገያዎች መኖራቸውን ያረጋግጣል፤ ይፈቅዳል፤ ይወናል፤ ይገመግማል፤ ይቆጣጠራል፤

2/ Conduct, in its own capacity, appraisal and quality assurance for any project or program for which a feasibility study has been conducted, and submit a feasibility assessment report to the Planning and Development Bureau;

3/ Revise projects approved for revision pursuant to the relevant laws and submit same to the Planning and Development Bureau, which shall in turn submit them to the Regional Government Council for decision;

4/ Prepare and submit a request for the revision of any project or program that exceeds the limits prescribed by law to the Planning and Development Bureau, which shall in turn submit it to the Government Council for decision;

5/ Ensure that the necessary preconditions for implementation are met before the implementation of a project or program that has been submitted for appraisal and approved;

6/ Prepare a project or program implementation plan based on the feasibility study for the selected and prioritized project or program and submit it to the Planning and Development Bureaue for decision;

7/ In accordance with the powers conferred upon them with respect to the formulation, appraisal, implementation and monitoring cycles of projects and programs:

A) Ensures that essential project and program tools are available, approves, decides on, evaluates and supervise same;

ለ) የፕሮጀክት ወይም የፕሮግራም የአገልግሎት እና የመሠረተ-ልማት ስታንዳርዶች ያወጣል፤ በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

፰/ በዓመታዊ በጀት ውስጥ የተካተተን ፕሮጀክት ቅደም-ተከተል ማስያዝ ወይም በበጀት በሚካተትበት ወቅት የቀረበውን የመጨረሻ የትግበራ እቅድ የበጀት ዓመቱ በተጀመረ በመጀመሪያው ወር ለገንዘብ ቢሮ እና ለፕላንና ልማት ቢሮ ያቀርባል፤

፱/ በስሩ ተግባራዊ እየተደረገ በሚገኝ ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ላይ የመደበኛ ክትትል እና ግምገማ ያደርጋል፣ የፕሮጀክት ወይም የፕሮግራም አፈፃፀም ሪፖርት ለገንዘብ ቢሮ እና ለፕላንና ልማት ቢሮ ያቀርባል፤

፲/ በስሩ ተግባራዊ እየተደረጉ በሚገኝ ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ዙሪያ የሚመለከታቸውን ተቋማት በማሳተፍ በዋና ዋና የትግበራ ምዕራፎች ላይ የአፈፃፀም ግምገማ ያደርጋል፤

፲፩/ በስሩ ወይም በተጠሪ ተቋማት ስር ያለ ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ሲጠናቀቅ የማጠናቀቂያ ሪፖርት በማዘጋጀት ለፕላንና ልማት ቢሮ እና ለገንዘብ ቢሮ ያቀርባል፤

፲፪/ አንድን ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም በተገባለት ውል መሠረት የታለመለትን ዓላማና ውጤት በሚያሳካ መንገድ መጠናቀቁን አረጋግጦ ይረከባል፤ ፕሮጀክቱ ወይም ፕሮግራሙ ወደ ምርት ወይም አገልግሎት መስጠት እንዲገባ ያደርጋል፤

፲፫/ በስሩ የሚገኝ የፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ሀብትን ይመዘግባል፣ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ወቅታዊ የሆነ መረጃ ያቀርባል፤

B) Issues project or program service and infrastructure standards and ensures their implementation;

8/ Prioritize projects included in the annual budget, or submit the final implementation plan prepared for budgeting to the Bureau of Finance and the Planning and Development Bureau within one month from the commencement of the budget year;

9/ Conduct regular monitoring and evaluation of a project or program which are being implemented under it; submit the project progress report to the Bureau of Finance and the Planning and Development Bureau;

10/ Conduct performance evaluations on key implementation phases of any project or program being implemented under it through involving the relevant institutions;

11/ Upon completion of a project or program undertaken by it or by institutions accountable to it, prepare a completion report and submit it to the Planning and Development Bureau and the Bureau of Finance;

12/ Hand over by ensuring wether a project or program is completed in a manner that achieves its intended objectives and results in accordance with the agreed-upon contract, and make the project or program to be brought into production or service provision;

13/ Register the assets of projects or prgrams under its control; provide up to date information to the relevant government body;

፲፬/ ተግባራዊ የተደረጉ ፕሮጀክቶችን ወይም ፕሮግራሞችን በተመለከተ እንደ አስፈላጊነቱ የድኅረ-ትግበራ ግምገማ ያከናውናል፣ በድኅረ-ትግበራ ግምገማ የተገኙ ግብዓቶችን በቀጣይ ለሚተገበሩ ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች ዝግጅት ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

፲፭/ ፕሮጀክቶች ወይም ፕሮግራሞች በክልል ደረጃ በተሟላ ሁኔታ በመረጃ ቋት እንዲያዙ የፕሮጀክት አፈፃፀም መረጃዎችን ለፕላንና ልማት ቢሮ ያቀርባል፤

፲፮/ በስሩ ወይም በተጠሪ ተቋማት ስር ያሉ ፕሮጀክቶችን ወይም ፕሮግራሞችን በተመለከተ ውል በሚያዘጋጁበት ወይም በሚዋዋሉበት ጊዜ በፍትሕ ቢሮ ወይም በፍትሕ ቢሮ የተዋረድ አደረጃጀቶች ተገቢውን የሕግ አስተያየትና ምክር እንዲሰጥበት ያደርጋል፤ የጸደቀውን ውል ያስመዘግባል፤

፲፯/ በሀገር ውስጥ ወይም በውጭ ብድር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ወይም ፕሮግራሞች በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን የፕሮጀክቶች ዑደቶች ጠብቀው መዘጋጀታቸውን ወይም ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

፲፰/ የፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ዝግጅት፣ ትግበራና ድኅረ-ትግበራ ሂደት ከመግባቱ በፊት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲከናወን ያደርጋል፤

፲፱/ በፕሮጀክቶች ወይም ፕሮግራሞች ዝግጅት እና ትግበራ ሂደት የአካባቢው ማኅበረሰብ ተሳታፊ መሆኑን ያረጋግጣል፤

፳/ በፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም አፈፃፀም መረጃ መሠረት በፕሮጀክቱ ወይም ፕሮግራሙ አካባቢ ለሚኖሩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ስለፕሮጀክቶቹ ወይም ፕሮግራሞቹ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ግንዛቤ ያስጨብጣል።

14/ Conduct post-implementation evaluations of implemented projects or programs as necessary, and ensure that the findings from such evaluations are utilized in the preparation of subsequent projects and programs;

15/ Provide project implementation information to the Planning and Development Bureau to ensure that projects are fully incorporated into a comprehensive regional database;

16/ Upon drafting or signing contracts relating to projects or programs undertaken by it or by institutions accountable to it, ensure that the Bureau of Justice or its subordinate bodies provide appropriate legal opinions and recommendations and that the approved contracts are duly recorded;

17/ Ensure that projects implemented through domestic or foreign loan mechanisms follow the project cycles specified in this Proclamation during their formulation and implementation;

18/ Ensure that an environmental impact assessment is conducted prior to the preparation, implementation and post-implementation stages of any project or program;

19/ Ensure the participation of the local community in the preparation and implementation of projects or programs;

20/ Based on the performance information of a project or program, raise awareness among community members residing in the project or program area regarding the importance and benefits of such projects or programs.

## ፲፰. የፕላንና ልማት ቢሮ ሥልጣንና ተግባራት

፩/ በፕሮጀክት አስፈፃሚ አካላት የሚቀርብ የፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ፅንሰ-ሐሳብ ይዘትን በመገምገም የመጀመሪያ ደረጃ የግምገማ ውሳኔ ይሰጣል፤

፪/ በመካከለኛ እና ከፍተኛ ፕሮጀክቶች ወይም ፕሮግራሞች ላይ የአዋጭነት እና አስፈላጊነት ግምገማ ያካሄዳል፣ ፕሮጀክቶችን ቅደም ተከተል ያስይዛል፣ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

፫/ የአዋጭነት ግምገማ ተደርጎባቸው አዋጭነታቸው የተረጋገጡ አዳዲስ ፕሮጀክቶች ወደ ካፒታል በጀት እንዲገቡ በክልሉ የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅድ መሠረት ይመርጣል፤ ቅደም-ተከተል በማስያዝ ለውሳኔ ለመስተዳድር ምክር ቤቱ ያቀርባል፤

፬/ በተመረጡ ስትራቴጂክ ፕሮጀክቶች ወይም ፕሮግራሞች ላይ ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፣ በፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም አፈፃፀም ላይ የታዩ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር የልምድ ልውውጥ ያደርጋል፣ ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

፭/ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በፕሮጀክት አስፈጻሚ አካላት ክለሳ ተደርጎባቸው ውሳኔ እንዲሰጥባቸው የቀረቡ ፕሮጀክቶችን ወይም ፕሮግራሞችን ገምግሞ ለውሳኔ ለመስተዳድር ምክር ቤቱ ያቀርባል፤



## 18. Powers and Duties of the Planning and Development Bureau

1/ Evaluates the content of concept notes submitted by project implementing bodies and provides a preliminary appraisal decision;

2/ Conducts feasibility and relavance assessments on medium and high-level projects or programs; prioritizes projects, presents them to the relevant body, monitors and evaluates their implementation;

3/ Selects new projects that have been appraised and confirmed to be viable for inclusion in the capital budget in accordance with the Region's medium-term development plan, and submits them to the Government Council for decision in their order of priority;

4/ Monitors and evaluates selected strategic projects or programs, shares experiences of best practices in project or program implementation by formulating same, and ensures their effective execution;

5/ Reviews projects or programs, in accordance with the relevant law, which have been appraised and submitted for decision by project implementing bodies, and submits them to the Government Council for decision;

፮/ በሕግ ከተፈቀደው በላይ በፕሮጀክት አስፈፃሚ አካላት የሚቀርብ የመካከለኛ ወይም ከፍተኛ ፕሮጀክቶች ወይም ፕሮግራሞች ክለሳ የበጀት ለውጥ የሚያስከትሉ ሲሆን የአዋጭነት ግምገማ በማድረግ ለውሳኔ ለመስተዳድር ምክር ቤቱ ያቀርባል፤

፯/ እንደ አስፈላጊነቱ የፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ዝግጅት፣ አዋጭነት ግምገማና ማፅደቅ፣ ትግበራ ሂደት የሚያስፈልጉ ሙያዊና ቴክኒካዊ ጉዳዮች ተሟልተው እንዲገኙ ሁኔታዎችን ያጠናል፤ ይወስናል፤ ያስተባብራል፤

፰/ የፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ፅንሰ-ሐሳብ፣ የአዋጭነት ጥናት፣ የአዋጭነት ግምገማ፣ የትግበራ ዕቅድ፣ የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ፣ የክለሳ እና ድኅረ-ትግበራ ግምገማን በሚመለከት መመሪያዎችን ያወጣል፤ ተፈፃሚነታቸውንም ያረጋግጣል፤

፱/ ፕሮጀክቶችን ወይም ፕሮግራሞችን የሚመለከቱ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት የሚደራጁበትን፣ የሚጠናቀሩበትና የሚሰራጩበት ሥርዓትና ይዘት ያዘጋጃል፤ ይወስናል፤ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

፲/ ዋና ዋና የፕሮጀክቶች ወይም ፕሮግራሞች መረጃዎች ተደራሽ በሆኑ የመገናኛ ዘዴዎች ድረ-ገጾችን ጨምሮ ወቅታዊነታቸውን ጠብቀው ለሕዝብ ይፋ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፲፩/ እንደ አስፈላጊነቱ በፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር ዙሪያ የአቅም ግንባታ ተግባራትን ያከናውናል::

6/ Conducts feasibility study and submits it to the Government Council for decision when revisions to medium- or high-level projects or programs submitted by project implementing bodies exceed the limits permitted by law;

7/ Studies, determines and coordinates, as necessary, the conditions for the availability of professional and technical issues necessary in the preparation, feasibility assessment and approval, and implementation processes of project or program,

8/ Issues directives regarding project concept notes, feasibility studies, project appraisals, implementation plans, progress monitoring and evaluation, revisions and post-implementation evaluations, and ensures their implementations;

9/ Prepares and determines the system and content for organizing, compiling, and distributing central database of projects or programs, and monitors their implementation;

10/ Ensures that information on major projects or programs is kept up-to-date and made publicly available through accessible media, including websites;

11/ Conducts capacity-building activities in project administration and management as necessary.

## ፲፱. የገንዘብ ቢሮ ሥልጣንና ተግባራት

፩/ አዋጭ ተብለው ለበጀት ዕጩ የሆኑ ፕሮጀክቶችን ወይም ፕሮግራሞችን ለመምረጥ እና ቅደም ተከተል ለማስያዝ እንዲችሉ የክልሉን የፋይናንስ ሁኔታ እና የብድር ጫና መሠረት በማድረግ ሙያዊ ምክር ይሰጣል፤

፪/ ከፕላንና ልማት ቢሮ የሚቀርብን የፕሮጀክቶች ወይም የፕሮግራሞች ቅደም-ተከተል የውሳኔ ሐሳብ መሠረት በማድረግ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በጀት ውስጥ ያካትታል፣ በየደረጃው እንዲፀድቁ ያደርጋል፤

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሚኖረው ተጨባጭ የፋይናንስ ሁኔታ አንፃር የፕሮጀክቶች ወይም የፕሮግራሞች የማሽጋሸግ ሥራ ሊሠራ ይችላል፤

፬/ ፕሮጀክቶች ወይም ፕሮግራሞች በረቂቅ ዓመታዊ በጀት በሚካተቱበት ወቅት የቀረበው የትግበራ እቅድ ከመጀመሪያ ደረጃ ክፍያ በፊት የመጨረሻ የትግበራ እቅድ መቅረቡን ይገመግማል፤ ያረጋግጣል።

፭/ በሕግ በተፈቀደው መጠን በመስተዳደር ምክር ቤቱ በሚሰጠው የፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ክለሳ ማሻሻያ ውሳኔ መሠረት ተፈጻሚ ያደርጋል፤

## 19. Powers and Duties of Bureau of Finance

1/ Provides professional advice, based on the Region's financial situation and debt burden, regarding the selection and prioritization of projects or programs deemed viable for budget consideration;

2/ Ensures that new projects are included in the budget in accordance with the priority of projects or programs based on the recommendation of the Planning and Development Bureau submitted therefrom;

3/ Without prejudice to the provision under Sub-article (2) of this Article, it may perform a readjustment activity of projects or programs based on the actual financial condition;

4/ Reviews and confirms the submission of final implementation plan prior to release of any initial payment of the implementation plan submitted when projects or programs were included in the draft annual budget;

5/ Implements project or program revisions approved by the Government Council to the extent permitted by law;

፮/ በሕግ ከተፈቀደው በላይ በፕሮጀክቶች አስፈፃሚ አካላት በሚቀርብ የመካከለኛ ወይም ከፍተኛ ፕሮጀክቶች ወይም ፕሮግራሞች ክለሳ ላይ በመስተዳደር ምክር ቤቱ ውሳኔ መሠረት ተፈፃሚ ያደርጋል፤

፯/ የፕሮጀክቶችን ፋይናንስ በበላይነት ያስተዳድራል፣ ተግባራዊ እየተደረጉ የሚገኙ ፕሮጀክቶችን በፕሮግራም በጀት ማዕቀፍ መደበኛ የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፤ የተጠቃለለ የክልል መንግሥት ፕሮጀክቶች ወይም ፕሮግራሞች ዓመታዊ የፋይናንስ አፈፃፀም ክትትል ሪፖርት ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ያቀርባል፤

፰/ ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ የሚገኙ ፕሮጀክቶችን ወይም ፕሮግራሞችን አስመልክቶ የሚደረጉ ስምምነቶችን የክልሉን የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ የፕሮጀክቶችንና ፕሮግራሞችን ፍላጎት መሠረት በማድረግ በክልሉ መንግሥት ስም ይፈራረማል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

፱/ የመንግሥት ፕሮጀክቶችን ወይም ፕሮግራሞችን የፋይናንስ አፈፃፀም መረጃ በማጠናቀር በመረጃ ቋት ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋል፤

፲/ በፕሮጀክቶች ዝግጅት እና ትግበራ ሂደት ላይ የአካባቢው ማኅበረሰብ ተሳታፊ እንዲሆን የሚመለከተው አካል የበኩሉን ኃላፊነት እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

6/ Implements, in accordance with the decision of the Government Council, on the review of medium or high-level projects or programs submitted by project implementing bodies beyond the limit permitted by law;

7/ Supervises project financing, conducts regular monitoring and evaluation of projects implemented under the program budget framework, and submits consolidated annual finance performance monitoring report of projects or programs of the region to the appropriate government bodies.

8/ Signs agreements, on behalf of the Regional Government, relating to domestic and foreign projects or programs in accordance with the Region's medium-term project and program needs, and monitors their implementation.

9/ Makes information of financial performance of government projects or programs to be consolidated and entered into a database;

10/ Ensures that the relevant body carries out its responsibility in the participation of the local community in the preparation and implementation of projects.

## ፳. የአማራ ክልል ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባር

፩/ በኮንስትራክሽን ሥራ እና ግንባታ አደጋ ሲፈጠር ምክንያቱን እና የጉዳት መጠኑን ያጣራል፣ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል፣ የሕግ ተጠያቂነት እንዲኖር ይሠራል፤

፪/ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች የዲዛይን ስታንዳርድ ያወጣል፣ የዲዛይን ግምገማ በኮንስትራክሽን ዲዛይን መሠረት መደረጉን ያረጋግጣል፣ ከኮንስትራክሽን ስታንዳርድ አኳያ ቁጥጥር ያደርጋል፤

፫/ በዘመናዊ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት አስተዳደር ዙሪያ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፤

፬/ የፕሮጀክት አስፈፃሚ አካላት በሚያቀርቡት የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ጥናት መሠረት ወደ ትግበራ ከመግባታቸው በፊት አስፈላጊ የመሠረተ ልማት ፋሲሊቲዎች መቀናጀታቸውንና መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤ ይከታተላል፤

፭/ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ትግበራ ላይ በመሠረተ-ልማት አቅራቢ ድርጅቶች መካከል ሊኖር የሚገባውን ቅንጅት እና አሠራር በተመለከተ ሙያዊ ምክር ይሰጣል፤ ቅንጅቱን በበላይነት ይመራል፤ ይከታተላል፤

፮/ ከፕሮጀክት አስፈጻሚ አካላት ጋር የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ውል በተገባበት ዲዛይን፣ ዋጋ፣ ጥራትና ጊዜ ተሠርተው ስለመጠናቀቃቸው እና ርክክብ ስለመደረጉ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤



## 20. Powers and Duties of the Amhara Region Construction Authority

1/ Where an accident occurs during construction works, investigates the cause and extent of the damage; submits a report to the relevant body, works for the presence of legal accountability;

2/ Issues design standards for construction projects, ensures that design evaluations are conducted in accordance with the construction designs, and monitors compliance with construction standards;

3/ Carries out capacity-building activities in the field of modern construction project management;

4/ Ensures and monitors that necessary infrastructure facilities are coordinated and fulfilled prior to implementation based on the construction project study submitted by the project implementing bodies;

5/ Provides professional advice on the coordination mechanisms and procedures to be applied among infrastructure development service providers in the implementation of construction projects; oversees and monitors such coordination;

6/ Monitors, controls and takes corrective measures to ensure that construction projects are completed and handed over in accordance with the agreed design, cost, quality and timeline with the project implementing bodies;

፯/ የመንግሥት ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት አፈፃፀም ከጊዜ፣ ከጥራትና ወጪ አንፃር ክንውኑን ኦዲት ያደርጋል፣ በሚገኙ ክፍተቶች የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

፰/ በክልሉ መንግሥት በጀት እና በግሉ ዘርፍ ለሚገነቡ ማናቸውም ግንባታዎች የሚያስፈልጉ ዲዛይኖችን መርምሮ ያፀድቃል፣ የግንባታ ፈቃድ ይሰጣል፣ ከፍትሕ ቢሮ ጋር በመሆን የመንግሥት የግንባታ ሥራ ውሎች በአግባቡ መዘጋጀታቸውን ክትትልና እና ቁጥጥር ያደርጋል፤

፱/ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ሥራዎች በአካባቢ፣ በሠራተኞች እና በኅብረተሰቡ ጤንነት እና ደኅንነት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ለመከላከል የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀማቸውን ይቆጣጠራል፤

፲/ የዲዛይን ለውጥን እና ተያያዥ ምክንያቶችን ተከትሎ የሚፈጠር ተጨማሪ የግንባታ ሥራዎች እና ተጨማሪ ዋጋ ሲያጋጥም የሚቀርብለትን ጥያቄ አጣርቶ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ ሲፈቀድለትም በሕጉ መሠረት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፲፩/ የክልሉ መንግሥት የሚያካሂዳቸውን የግንባታ ፕሮጀክቶች የጨረታ ሁኔታ ግምገማ ያካሂዳል፣ በሴክተሮች የሚቀርብለትን የጨረታ ውጤት በመመርመር ያረጋግጣል፡፡

7/ Audits the performance of government construction projects with respect to time, quality and cost, and takes corrective measures where gaps are identified;

8/ Examines and approves designs required for any construction projects funded by the Regional Government budget and the private sector, issues construction permits, and, in coordination with the Bureau of Justice, monitors and ensures proper preparation of government construction contracts;

9/ Establishes and monitors the implementation of a system of procedures to prevent construction project activities from causing harm to the environment, workers, and the health and safety of the society;

10/ Investigates requests for additional construction works and costs arising from design changes or related factors and submits them to the relevant body; upon approval, causes implementation of same in accordance with the law;

11/ Conducts tender evaluations of construction projects undertaken by the regional government, verifies the results of tenders submitted by sectors through examining thereof.

## ፳፩. የፍትሕ ቢሮ ሥልጣንና ተግባራት

፩/ የመንግሥት ፕሮጀክቶች ፈፃሚ አካላት በስራቸው ያሉ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ውል በሚያዘጋጁበት ጊዜ ተገቢውን የሕግ አስተያየትና ምክር ይሰጣል፤

፪/ የሕዝብ ወይም የመንግሥት ጥቅም ይጎዳል ብሎ ሲያምን ከፕሮጀክት አስፈፃሚ አካላት ጋር በመሆን የውል ዝግጅትና ድርድር ያደርጋል፤

፫/ የፕሮጀክት አስፈጻሚ አካላት ከሌሎች ተዋዋይ ወገኖች ጋር የፈጸሟቸውን የፕሮጀክት ውሎች መርምሮ ይመዘግባል፤ በአግባቡ ሰነዶ ይይዛል።

## ፳፪. የመሬት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

፩/ ለፕሮጀክቶች መሬት ያቀርባል፤

፪/ በፕሮጀክቶች ምክንያት ለሚነሡ ማኅበረሰቦች አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ካሣ እንዲከፈል ተቀናጅቶ ይሠራል፤

፫/ በፕሮጀክቶች ምክንያት ለሚነሡ ማኅበረሰቦች አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የካሣ ክፍያ እና ሌሎች ጥያቄዎች የሚስተናገዱበትን የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

፬/ በፕሮጀክት ዝግጅትና ትግበራ ሂደት ላይ የአካባቢው ማኅበረሰብ ተሳታፊ እንዲሆን የበኩሉን ኃላፊነት ይወጣል።

## ፳፫/ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባራት

ማንኛውም የፕሮጀክት አስፈጻሚ አካል የፕሮጀክት ዝግጅት፣ ትግበራና ድኅረ-ትግበራ ሂደት ውስጥ ከመግባቱ በፊት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲከናወን ያደርጋል፤ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ሙያዊ እገዛ ይሰጣል።

## 21. Powers and Duties of the Bureau of Justice

1/ Provides appropriate legal opinions and advice to government project implementing bodies in the preparation of contracts for projects under their control;

2/ Prepares and negotiates contracts, in collaboration with project implementing bodies, whenever it appears that the public or government interests may be adversely affected;

3/ Reviews and records project agreements entered into by project implementing bodies with other parties, and ensures proper documentation of the same.

## 22. Powers and Duties of the Land Bureau

1/ Provides land for projects;

2/ Works coordinatedly so that communities affected by projects are compensated in accordance with applicable laws;

3/ Establishes a mechanism for handling compensation and other claims of communities in relation to eviction for projects, in accordance with applicable law;

4/ Carries out its responsibility in the participation of the local community in the preparation and implementation of projects.

## 23. Powers and Duties of Environmental Protection Authority

Conducts an environmental impact assessment before commencing project preparation, implementation and post-implementation processes by any project implementing body; establishes procedures and provides professional assistance for the same.

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፳፬. የመተባበር ግዴታና ተጠያቂነት

፩/ ማንኛውም ሰው ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ ድንጋጌ ተላልፎ ቢገኝ እንደየአግባቡ አስተዳደራዊ፣ ፍትሐብሔራዊና የወንጀል ተጠያቂነት ይኖርበታል፡፡

### ፳፭. ደንብ ስለማውጣት

የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ለአዋጁ አፈፃፀም የሚረዳ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

### ፳፮. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም ልምዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

### ፳፯. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት ወደ ትግበራ የገባ ፕሮጀክት ሲሠራበት በነበረው ሥርዓት መሠረት ፍፃሜ ያገኛል፡፡

### ፳፰. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባሕር ዳር
መጋቢት 25 ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም
አረጋ ከበደ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ፕሬዚዳንት



## PART FIVE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 24. Duty to Cooperate and Accountablity

1/ Every person shall have the obligation to cooperate in the implementation of this Proclamation.

2/ Any person found to have violated the provisions of this Proclamation shall be subject to administrative, judicial, or criminal liability, as appropriate.

### 25. Issuing of Regualtion

The Regional Government Council may issue Regulation necessary for the implementation of the Proclamation.

### 26. Inapplicable Laws

No law or customary practice inconsistent with this Proclamation shall have effect with respect to matters covered in this Proclamation.

### 27. Transitory Provisions

Any project implemented prior to effective date of of this Proclamation shall be completed in accordance with the system applicable at the time of its implementation.

### 28. Effective Date

This Proclamation shall enter into force since the date of its publication in the regional Zikrehig Gazette.

**Done at Bahir Dar,**
**This 3rd date of April, 2026.**
**Arega Kebede**
**President of the Amhara National Regional State.**